Oromia Bank
Baankii Oromiyaa ኦሮሚያ ባንክ

# የጉባኤ ጥሪ ማስታወቂያ
# ኦሮሚያ ባንክ አክሲዮን ማህበር
# የባለአክሲዮኖች 16ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የጉባኤ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1)፣367(1)፣ እና 370፤እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ (ባንኩ) መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 14(5) መሰረት፤ የኦሮሚያ ባንክ አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች 16ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ህዳር 27 ቀን 2018 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ በሚሊንየም አዳራሽ ይካሄዳል፡፡ በመሆኑም የተከበራችሁ የባንኩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባኤው ላይ እንድትገኙ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

## 1. ባንኩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

**1.1.** የባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ፡-አዲስ አበባ፣ ክ/ከተማ፤ ቂርቆስ፣ ወረዳ፤01፤የቤት ቁጥር፤407

**1.2.** የባንኩ የምዝገባ ቁጥር፡- KK/AA/3/0007345/2007

**1.3.** የባንኩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፡- ........................7,820,633,000

**1.4.** የባንኩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፡- ..........................6,925,127,000

## 2. የ16ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

**2.1.** እስከ ህዳር 26 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ የተፈፀሙ የአዳዲስ አክሲዮኖች ሽያጭና የነባር አክሲዮኖች ዝውውር ላይ ተወያይቶ መወሰን፣

**2.2.** እ.አ.አ የ2024/25 የሂሳብ ዓመት የዳይሬክተሮች ቦርድን ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ፣

**2.3.** እ.አ.አ የ2024/25 የሂሳብ ዓመት የባንኩን የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ፣

**2.4.** የ2024/25 የሂሳብ ዓመት የተጣራ ትርፍ አደላደልና አከፋፈልን አስመልክቶ በቀረበው የውሣኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣

**2.5.** እ.አ.አ ለ2025/26 በጀት ዓመት የሚያገለግሉ የውጭ ኦዲተሮችን ሹመት ማጽደቅና አበላቸውን መወሰን፣

**2.6.** እ.አ.አ የ2025/26 የዳይሬክተሮች ቦርድን ወርሃዊ አበል እና እ.አ.አ በ2024/25 ባንኩ ካገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ ለቦርዱ የሚሰጥ ዓመታዊ ጉርሻ (Compensation) ላይ ተወያይቶ መወሰን፣

**2.7.** የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን በዕጩነት ለማቅረብና ለመምረጥ በቀረበው ፖሊሲና የአፈፃፀም መመሪያ ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ፤

## 3. ማሳሰቢያ

3.1 በጉባኤው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻቸው ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ ውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በኢፌዲሪ ንግድ ህግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀናት በፊት በባንኩ ዋና መስሪያ ቤት ወይም በአቅራቢያቸው በሚገኙ የባንኩ ቅርንጫፎች በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በቦርዱ የተዘጋጀውን የውክልና ቅጽ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡ ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

3.2 የባንኩ ባለአክሲዮኖች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባኤው ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

3.3 በሥራ ላይ ያሉ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትና የባንኩ ሰራተኞች ሌሎች የባንኩን ባለአክሲዮኖች ወክለው በጉባዔው ላይ መሳተፍ የማይችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የኦሮሚያ ባንክ (አ.ማ) የዳይሬክተሮች ቦርድ**